# የመሬት ለውጦች ሕልም

## The Dream of Earth Changes

### በሱዛን ከሚንግስ

By *Susan Cummings*

ትላንትና ማታ በሕልም፥ ጌታ ወደ ሰማያት ወሰደኝ። የሆነ ቦታ ቆሜ ነበር፥ የት እንደሆነ ግን አላውቅም። ነገር ግን ቆሜ ወደ ምድር እያየሁ ነበር። ከፊት ለፊቴ ሆኖ አየሁት። ጌታ እየገለጠ (revealing) ያለውን አንድ ነገር እንዳይ ወደዚህ አመጣኝ።

እያየሁት ሳለ፥ መላ መሬትን ሊመታ ያለ መብረቅ በተለያዩ አካባቢዎች መሬትን መምታት ሲጀምር አየሁ። ታላቅ የመብረቅ ማእበል ሆነ መሬትም በመብረቅ ተሸፈነች። በጣም የሚያስፈራና ሲያዩት የሚያስደንቅ ነበር ነገር ግን በምድር ላይ በጣም አውዳሚ ነበር።

ከዚያም ከጥቂት ቆይታ በኋላ፥ በምድር ላይ መዝነብ ጀመረ፥ ታላቅ ዶፍ ዝናብ። በተለምዶ ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎችም ጭምር አሁን በኃይል እየዘነበባቸው ነው እናም ዝናቡ ብዙ አካባቢዎችን በጎርፍ አጥለቀለቀ።

ቀጥሎ ሌላ እይታ፥ ብዙ እሳተጎመራዎች ሲፈነዱና ምድር በአንዳንድ አካባቢዎች የተከፈተች ጥልቅ ስትሆን። በአንዳንድ አካባቢዎች መሬቶች እየተከፈቱ እሳትን ይተፋሉ። የመሬት መንቀጥቀጦች ታላቅ የሆነውን ግፊት ለቀቁት በብዙም ቦታዎች መላው የመሬት ገጽታ ተናወጠ ተቀያየረም።

ቀጥሎ ሌላ እይታ ደግሞ መጣ። በመሬት ላይ እሳት መዝነብ ጀመረ። እሳት በየቦታው ይዘንብ ነበር። በብዙ አካባቢዎች እሳት በየቦታው ይነድድ ነበር። የእሳቱ ድምጽ ይሰማኝ ነበር እናም እንደ አንበሳ ግሳት ነበር። አስፈሪና ታላቅ ነበር። የሚባላ እሳት ነበር።

ቀጥሎ ሌላ እይታ። በዚህ ጊዜ ታላቅ ንፋስ በምድር ላይ ነፈሰ። ምድርን ያናወጠና የሸፈናት ንፋስ ነበር። በዚህ ንፋስ ምንም የቆመ አልነበረም። ሁሉም ወደታች (ዝቅታ) ተወሰደ። ንፋሱ እያፏጨና በምድር ላይ እየሮጠ ነበር እናም ታላቅ ጥፋት ሆነ። ንፋሱ ሲያቆም ከነበርሁበት ስፍራ ሆኜ ምንም ነገር ምንም የቀረ የሚታየኝ ነገር አልነበረም።

ሁሉም ባዶ ነበረ።

እየተመከትሁ ሳለ፥ የምድር ወለሎች ተሰነጣጥቀው ሲከፈቱና ታላቅ አስደናቂ ብርሃን ከምድር ውስጥ መውጣት ሲጀምር አየሁ። ምድር መከፋፈል እየጀመረች እንደሆነ፥ እንዲሁ አወቅሁ፥ ነገር ግን እየተፈጠረ ያለው እንዲሁ ነበር።

ከዚያም ሕልሙ አለቀና ሌሊቱን ሙሉ ሲደጋገም ነበር።

-ሱዛን ከሚንግስ፥ እ.ኤ.አ ሴፐቴምበር 20፥2005 ዓ.ም

"በመግረክ ደጆች ውስጥ" ከሚለው ከሱዛን ከሚንግስ ራእይ ውስጥ፤

በራእይ አንድ እይታ በፊቴ ሲዘረጋ አየሁ። የጥንታዊ ከተማ ወይም መንደር እይታ ነው። ይህን መንደር የከበቡት የድንጋይ አጥሮች ነበሩ፥ አጥሮቹም ጥቅጥቅ ያሉና ረዥም ነበሩ። ድንጋዮቹ የጥንት ሲሆኑ በስንጥቆቻቸውም መሀከል እጽዋት እየበቀሉባቸው ነው።

እይታው ወደ ቀኑ ማለቂያ አካባቢ ነው፥እናም ረፍዷል። አንዳንድ ሰዎች በከተማዋ አጥር ዙሪያ ተቀምጠው አየሁ። አንዳንዶች ከከተማ አጥር ውጪ ዳሶችን ጥለው በእሳት ዙሪያ ተቀምጠዋል፥ ጥቂቶች ደግሞ ወደ ሌላኛው የአጥሩ አቅጣጫ ለመሄድ እየዞሩ ነው። በሌላኛው አቅጣጫ በኩል ምን እንዳለ አይታየኝም፥ሰለዚህ በፊቴ የተዘረጋውን እይታ ማየት ቀጠልሁ።

ለጥቂት ደቂቃዎች አጥሮቹን አጠናሁ። አስቀድሞ እንዳስተዋልሁት፥አጥሮቹ አርጅተዋል። በጣም ረጃጅምና ሰፋፊ ናቸው እናም በየቦታው ክፍተት አለባቸው፥ እንደ መስኮት ይመስለኛል። አጥሩ በዚህ በኩል ከአንድ በጣም ካረጀና ሙሉ በሙሉ በዙሪያው በበቀሉ እሾህማ ቁጥቋጦዎችና ሌሎች ነገሮች ከተዘጋ በር በቀር ምንም ዓይነት መግቢያ የለውም።

ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ሰዎቹ ወደ አጥሩ ሌላኛው ጎን እየሄዱ ያሉት። ይሄኛውን በር ማንም ሰው አጥርቶትም ሆነ ገብቶበት የሚያውቅ አይመስልም። በዚህ የአጥሩ አቅጣጫ ያለው ብቸኛው ነገር፥ እዚህም እዚያም የሰፈሩት ሰዎችና የበቀሉት ቁጥቋጦዎች ናቸው።

ጓጉቼ ነበርና ይህንን በር ማየት ፈለግኹ። ልክ ስለዚህ በር ሳስብ፥በቅጽበት፥በራእዩ ውስጥ ወደ በሩ ቅርብ ተወሰድሁ።

በሩ በእርግጥም በጣም ብዙ አትክልት በቅሎበት ለማየት አስቸጋሪ ነው። እኔ ራሴ፥ ቁጥቋጦዎቹን ተሻግሬ ከመግባቴ በፊት ሁለት ጊዜ ማሰብ ይጠበቅብኛል። ከበሩ ላይ ሙሉ በሙሉ ለማጽዳት ከሞከራችሁ ቦጫጭሮ ነው የሚያስቀራችሁ። በቁጥቋጦው ውስጥ አልፌ ስፈልገው በሩ ዝግ ነበር። በጣም ከባድ በር ሲሆን እስካሁን ድረስ መክፈቻው ላይ ተሰክቶ ያለ ትልቅ ቁልፍ አለው። ማንም ሊነቅለው እንኳ አልሞከረም።

ከዛ በራሴ ሳቅሁ፥በዙሪያው ይሄ ሁሉ ነገር በቅሎ፥ ማንም ሊያነሳው አይችልም! በሩን እያየሁ በዚያ ቆምሁ። ከዚያም ከበሩ በላይ ጽሑፍ አየሁ። አንዳንዶቹ ሐረጎች በላዩ ላይ ስለበቀሉ ለማንበብ ከባድ ነበር። ነገር ግን ተንጠራርቼ የተወሰኑትን ቅርንጫፎች በጣጠስኳቸው። ጽሑፍ በጣም የድሮና በበሩ አናት ላይ ባለ ድንጋይ ላይ የተቀረጸ ነበር። እንዲህ ይላል፡"ተማረኩ።" "Surrender."

ወደ ኋላ ተጠጋሁና ምን ያህል ጊዜ ይሆነው ይሆን ብዬ አሰብሁ። ማን ሥራው ለምንስ ለረዥም ጊዜ ጥቅም ላይ አልዋለም። ማንም ሰው ለምን መንገዱን እንዳላጠራውና በሩን እንዳልተጠቀሙበት አሰብሁ ምክንያቱም ወደ ከተማዋ ያስገባቸው ነበር።

ከዚያም ጌታ ተናገረኝ፥"*መማረክ ከሁሉም በሮች ውስጥ ጥቂት ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ በር ነው።*"

ዞር ስል ጌታ ከአጠገቤ ቆሞ ነበር። ወደ በሩ እየጠቆመ ነበር።

እንዲህ አለ፡ "***ይህ መግቢያ ከሁሉም ይልቅ ዋጋ ያለው ነው፥ እንዲሁም በጥቂቱ ብቻ የሚታወቅ። በጣም የሚጠላና በጣም የሚፈራ ነው፥ እናም ሰዎች በዚህ ላለመግባት ምንም ነገር ያደርጋሉ፥ ምንም እንኳ ወደ ከተማዋ ለመግባት ፈጣኑ በር ቢሆንም።***"

"***እንደገመትሽው፥ ይህ ከተማ ቤቴን ይወክላል፥ እንዲሁም አሁን ያለበት ሁኔታ በተመሰቃቀለና እድሳት በሚያስፈልገው ሁኔታ ውስጥ መሆኑን። ደጆቹ ብዙ ናቸው፥ ነገር ግን በጣም አስፈላጊዎቹ ብዙውን ጊዜ***

*ይጨቆናሉ፥ቸል ይባላሉ፥ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፥ወይም ይሰበራሉ። ብዙውን ጊዜ የሚያገለግሉት በሮች ወደ ንግዳቸው (ሥራቸው) ወይም ወደ ጋራ መሰባሰቢያ ስፍራቸው የሚወስዱት ናቸው።"*

ከዚያም በሐረጎቹ መሀከል አለፈና አንዱን በእጁ ወሰደ።

እያመለከተ እንዲህ አለኝ፡ "*በዚህ በር መግባት ትችያለሽ?*" ጭንቅላቴን አነቃንቅሁና፥ "*መጀመሪያ መንገዱን ሳላጠራ አልችልም*" አልሁት።

ጌታ በብዙ ፈገግ አለ። "*አዎን*" አለኝ፥ "*ይህን ነው እያደረግሁ ያለሁት።"*

"*ብዙዎች ይህን በር (ትተው) ማለፍ እንደሚችሉ ያስባሉ፥ እናም እኔ አሁን እያደረግሁት ወዳለሁት ለመግባት፥እናም በሌላ መንገድ ለመሄድ። ሰው ሊገባበት የሚችል ሌላ በር የለም። <u>በሩ እኔ ነኝ</u>፥እናም ወደ አብ የሚመጣ፥በዚህ ውስጥ ብቻ ነው ማለፍ የሚችለው። ለእኔ ሙሉ በሙሉ በመማረክ፥ያኔ በእውነት መግባት ይችላሉ።"*

"*ስለመዳን ብቻ አይደለም እያወራሁ ያለሁት። በብዙ ማስማሪያዎች ብዙ በጎች አሉኝ።"*

"*ሙሉ በሙሉ በእኔ ስለመሆን ነው እያወራሁ ያለሁት። መማረክ (መሰጠት) የሚመጣው ሁሉንም ነገር የእውነት በመጣልና ቀንበሬን በላያችሁ በመሸከም ነው፥ እናም ከጽዋዬ በመጠጣት። ጥቂቶች ይችላሉ። ብዙዎች ስሜን፥ደሜን፥ቃሌንና ዙፋኔን ይወስዱና የራሳቸው ያደርጉታል። ነገር ግን ጥቂቶች ብቻ የእውነት ሞተዋል ራሳቸውንም ከእግሬ በታች ጥለዋል፥ እናም በእኔ መልክ እንድሠራው ህይወታቸውን ሰጥተውኛል። ጥቂቶች እኔን ለመምሰል፥እንደ እኔ ለማሰብ፥እንዲሁም እንደ እኔ ለመኖር ይፈልጋሉ። የባሰ ጥቂቶች ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለእኔ ተሰጥተዋል።"*

"*የምመጣው የእኔ ለሆኑት ነው። ሙሉ በሙሉ ለእኔ ለተሰጡት፥ መከራን እየተቀበሉ ለሚኖሩት። የምመጣው መስቀሌን ለሚሸከሙትና ከጽዋዬ ለሚጠቱት ነው። የምመጣው መከራዬንና ደስታዬን (ሐሤቴን) ለሚያውቁት ነው። የምመጣው ጠባሳዬንና ስሜን ለሚሸከሙት ነው። በእርግጥም ቃሌንና ስሜን በሕዝቤ በልባቸውና በአእምሮአቸው ጽላት ላይ እጽፈዋለሁ። ልባቸውንና አእምሮአቸውን ለእኔ ለሰጡት፥ እናም በመንገዴ ሙሉ በሙሉ ለሚሄዱት። እነዚህ የሰዎችን ነቀፋ በሰውነታቸው የሚሸከሙና በውስጣቸውም ቅድስናዬን የሚጠብቁም (የሚይዙ) ናቸው። የአባቴ ሥራ በውስጣቸውና በውጫቸው እንዲቀጣጠል ፈቅደዋል። እነዚህ የእውነት ጻድቃኖች ናቸው።"*

ኢየሱስም ከዚያ በኋላ ወደ ኋላ ቆም አለና እኔ ወደ ቆምሁበት ተጠጋ። ተመለከተኝና፡ "*በበሩ እንድትገቢ እፈልጋለሁ፤*" አለኝ።

ዞር ብዬ በሩን ተመለከትሁት፥ እንዲሁም ወደ ቁጥቋጦዎቹ። ዋጥ አደረግሁና፥ "*እሺ። መንገዱን አጸዳለሁ። ሌሎች እንዲያልፉበት መንገዱን አጠራለሁ*" አልሁት።

ከዚያም ተመለስሁና ወደ ቅርንጫፎቹ ዘረጋሁ። ሳብኳቸው ነገር ግን ቅርንጫፎቹ በቀላሉ አልተንቀሳቀሱም። ቁጥቋጦዎቹ አይነቃነቁም። እዛው የደነዘዙ ይመስላሉ። በጣም ጠንካሮች ነበሩ፥ እናም ከጊዜ ብዛት፥ ከመሬቱ ጋር ጠልቀው የተጣበቁ። ይህ ከባድ ሥራ ነው የሚሆነው።

ከቁጥቋጦዎቹ ጋር እየታገልሁ ቅርንጫፎቹን ላስወግድባቸው የምችላቸውን መንገዶች አሰብሁ። ምንም የሚታየኝ መንገድ አልነበረም። ለመቆፈሪያ የሚሆን ነገር ፍለጋ በዙሪያዬ ተመለከትሁ። ከስራቸው ነቅዬ ባወጣቸው፥እያንዳንዱን ቁጥቋጦ አንድ በአንድ መሳብ እችላለሁ ብዬ አስብሁ። ነገር ግን ምንም አልነበረም። ጌታ አሁን እዚያው ቆሞ ነበር፥እርሱም ደግሞ ምንም አካፋ አልያዘም።

ጌታ በትኩረት ተመለከተኝ። መረበሽ እየጀመርሁ ነበር፥ እናም ቆምሁ። ቁጥቋጦዎቹ አለመነቃነቅ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን እየቦጫጨሩኝና እየሞነጫጨሩኝ ነበር። ምንም መሻሻል (ለውጥ) አላመጣሁም። ቁጥቋጦዎቹን ተመለከትሁና ተቀመጥሁ።

ቀና ብዬ ወደ ግርግዳው ተመለከትሁ፥ በአካባቢው ከስራቸው ከትቶ ለመፈንቀያ የሚሆን ምንም ነገር አልነበረም። ምንም ቦርድ (ጠፍጣፋ ነገር)፥ምንም ነገር አልነበረም። ትንሽ ራቅ ብለው የሰፈሩ ጥቂት ሰዎች ነበሩ፥ ነገር ግን ዝም ብለው ነበር የሚያዩኝ። “*እኔን ለመርዳት ምንም ፍላጉት የላቸውም*” ብዬ ለራሴ አሰብሁ።

ጌታ ከአጠገቤ ተቀመጠ። እንዲህ አለኝ፡ “*በራስሽ ሥራዎች ልትነቅዪአቸው አትችይም።*”

“*ሰዎች የሚሳሳቱት በሥራቸው ወደ እኔ ለመምጣት ስለሚያስቡ ነው። ህይወታቸውን ሊያጠሩና ሊያነጹ እንዲሁም ነገሮችን በራሳቸው መንገድ ሊያስተካክሉ ይችላሉ። ወደ ራሳችሁ መጨረሻ ስትመጡና ምንም ማድረግ እንደማትችሉ፥ እንዲሁም ያለ እኔ ምንም እንዳልሆናችሁ ስታውቁ ብቻ ነው ሙሉ በሙሉ ለእኔ የምትሰጡት (የምትማረኩት)። ነገር ግን ሰዎች ፈቃዳቸውን ሊሰጡኝ አይፈልጉም።*”

“*እኔ ብቻ ነኝ እሾኾቹን ልነቅላቸው የምችለው። ሰዎች ወደ እኔ እንዳይቀርቡ የሚከለክላቸው በራሳቸው ያቆሟቸው መከላከያዎች ናቸው። እያንዳንዱ እሾህ (ቁጥቋጦ) ጥበቃ፥ ምቾትና ብርታት የሚሰጧችሁን ነገሮች ይወክላሉ። በራስ መተማመናችሁን ይመግቡታል እናም ሙሉ እንደሆናችሁ እንድታስቡ ያደርጓችኋል። ለመመገብና ማንነቱን ለመጠበቅ የምትደገፉባቸው ነገሮች እነዚህ ነገሮች ናቸው።*”

“*እኔ የእውነት ጌታችሁ እንደሆንሁና እናንተ ከእኔ የተለያችሁ (የተነጠላችሁ) እንዳልሆናችሁ፥ እንዲሁም ፈቃዳችሁ ፈቃዴ እንደሆነ ስተረዱ ብቻ ነው፥ያኔ በህይወታችሁ ውስጥ ያሉትን እሾኾች (ቁጥቋጦዎች) ለእኔ ትተዋቸዋላችሁ። እስከዚያው ድረስ፥ ታቀኗቸዋላችሁ ለራሳችሁም አላማ ትጠቀሙባቸዋላችሁ እናም እኔ ለህይወታችሁ ያለኝ ፈቃድ ታጡታላችሁ። እኔን በጥልቀት እንዳያውቁኝ የሚያደርጓቸውን ቁጥቋጦዎችና መከላከያዎች ሁሉ ሊያስወግድ የሚችለው የእኔ እሳት ነው። የሚቀሩትንም ትርፍራፊዎች ሊያቃጥላቸው የሚችለው የእኔ እሳት ነው፥ከዚያም በሩን ለመክፈትና ከእኔ ጋር በነጻነት ለመራመድ ትችሉ ዘንድ።*”

ተነሳሁና ወደ ቁጥቋጦዎቹ ሄድሁ። ተመለከትኳቸውና ቅርንጫፎቻቸው ተጠላልፈው የተቆጣጠሩባቸው ቦታዎች ነካኋቸው። ከዚያም “*ጌታ ሆይ፥ ሙሉ በሙሉ ለአንተ እገዛለሁ (እሰጣለሁ)። እሳትህን አምጣና ትርፍራፊዎቹን ሁሉ፥ መከላከያዎቹን ሁሉ፥ ማንነቴን ሁሉ፥ የገዛ ፈቃዴን ሁሉ አቃጥላቸው። እኔ ያለአንተ ምንም ነኝ።*”

በድንገት ቁጥቋጦዎቹ ሁሉ በፊቴ መቃጠል ጀመሩ። ተቀጣጠሉና ተንቦገቦጉ። ወደ ኋላ አልኩና ሲቃጠሉ አየኋቸው። ቁጥቋጦዎቹ ቅጠሎቻቸውና ቅርንጫፎቻቸው ሲነዱ በእሳቱ ውስጥ ተሰባበሩ። ሲቃጠሉ እያየኋቸው የሚሰማኝ የሰላም ስሜት ነበር። እዚህ እዚያም እንደ ከሰል ፍርክስካሽ ሆነው ተቃጥለው ሲወድቁ አየኋቸው።

ከዚያም እየተቀጣጠሉ ባሉት የእሳት ፍርክስካሾች መሀል ተራመድሁና ወደ መግቢያው ሄድሁ። በሩ ዝግ ነበር መክፈቻውም እዛው በአሮጌው ቁልፍ ላይ ነበረ። በእርግጥም ከባድ በር ነበር። በጣም ትልቅ ነበር፥ እንዲሁም አሮጌ፥ ዙሪያውን እንደመቀነት የተዘረጋ ብረት ነበረው። መክፈቻው ትልቅ አሮጌ ቁልፍ ነበረ እናም መሀሉ ላይ ክብ ቀዳዳ ያለው ድቡልቡል መያዣ ነበረው። በቀዳዳው እጄን ከተትሁ።

እጆቼ በቀዳዳው ውስጥ በትክክል ይገጥማሉ። ቁልፉን ያዝሁና ማዞር ጀመርሁ። አይዞርም። በመቆለፊያው ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይቷል። የተቀረቀረ (የማይላቀቅ) ይመስላል። ከመቆለፊያው ውስጥም አይነቀልም። ለደቂቃ አሰብሁ። ቁልፉ ምንድ ነው? ከዚያም፥ ደህና፥ በደሙ በኩል እንገባለን፥ ብዬ አሰብሁ። ስለዚህም

"ሙሉ በሙሉ እንድገባና *ከእርሱ ጋር በጥልቀት እራመድ ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም አንጽቶኛል*" አልሁ።

ቁልፉ ዞረ መቆለፊያውም ድምጽ ሰጠ፥ እኔም በሩን ነካሁት። በእኔ ላይ ነግሦ የነበረ ትልቅ በር ነበር እናም ሲከፈት ብዙ ሰዎች በውስጡ መግባት ይችላሉ። ከዚያም ጌታ እንዲህ አለ፡ "*ሰው ሁሉ የሚገባበት በሩ እኔ ነኝ፥ በሩን ለሁሉም ሰው አቅርቤአለሁ። የሚፈልጉትን ሁሉ ለማሳለፍ ፈቃደኛ ነኝ፥ ነገር ግን የሚመርጡት ጥቂቶች ናቸው።*"

"*ብዙዎች በዚህ በር ዙሪያ ይሄዳሉ እናም ወደ ቤቴ ለመግባት ሌላ መንገድ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ስር (ዋና) የሆነውን ጉዳይ፥ እሾኾቹን፥ ፈጽሞ አይጋፈጡትም (የሆነ ነገር አያደርጉትም)፥ እናም ሙሉ በሙሉ ለእኔ የተሰጡ አይደሉም፥እናም ፈቃዳቸውን ለእኔ አልሰጡኝም፥ስለዚህ እኔ የእውነት ጌታ አይደለሁም።*"

"*ወደ እኔ የሚመጣውን እያንዳንዱን ልጅ እወስዳለሁ፥ እናም እያንዳንዳቸውን፥ አንድ በአንድ፥ በደጆቹ ወደቤቴ አመጣቸዋለሁ። እያንዳንዳቸው እውነትን ይይዛሉ፥ለህይወታቸውም ቁልፍን። እያንዳንዱም ወደ እኔ ያቀርባቸዋል እንዲሁም ጥልቅ የሆነን የእኔን እውቀት ያመጣላቸዋል፥ ነገር ግን ከዚህ ውጪ ምንም ነገር ሊያቀርባቸው ወይም ከእኔ ጋር ጥልቅ ወደ ሆነ ፍቅር ሊያመጣቸው አይችልም። ይህ እጅግ ተቃውሞ የበዛበትና እጅግ የሚፈራ ነው።*"

"*ሙሉ በሙሉ ለእኔ ካልተማረካችሁና ከእኔ ጋር አንድ ካልሆናችሁ፥ እንዲሁም እኔን መምሰልንና ህይወቴን በራሳችሁ ካልያዛችሁ፥ እንደዛ ካልሆነ እኔ የእውነት አላውቃችሁም። ሙሉ በሙሉ እስካልተለወጣችሁ ድረስ፥ እንግዳ እንደሆናችሁ ትቆያላችሁ፥እናም በምመጣበት ጊዜ ወደ ውጪው ጨለማ ትጣላላችሁ።*"

"*ሰዎች በእውነቴ ላይ ዳስ መጣል እንደሚችሉ ያስባሉ፥ እናም ከዚህም ከዚያም ጥቂት ነገሮችን መካፈል የሚችሉ፥ እናም መርሆአቸውና መከላከያቸው ያደርጉታል፥ ነገር ግን እኔን ሕያውን ቃል ሙሉውን የእግዚአብሔርን ምክር ወደህይወታቸው ለማካተት ይሳናቸዋል፥ እናም ሙሉ በሙሉ አልተለወጡም። በሥራዎቻቸው የበለጠ ይጠመዱና ከእኔ የባሰውኑ የተለዩ ይሆናሉ።*"

"*ነገር ግን እኔን ሙሉ በሙሉ ልታፈቅሩኝ፥እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ራሳችሁን እኔ ላይ ልትጥሉ ያስፈልጋል፥ እናም ሙሉ በሙሉ እንደ ጌታችሁና አምላካችሁ ልትወስዱኝ ይገባል። እኔ ብቻ ነኝ እንደ እኔ አምሳያ የማደርጋችሁ፥ እንደራሳችሁም አይደለም። አንዱን እውነት ወስዳችሁ ሌላውን እውነት አትተዉ፥ ነገር ግን ቃሎቼን ሁሉ እኩል ውደዷቸው፥ በእናንተ ውስጥም ሥራውን ይሥራ። አንዱን እውነት ከሌላው እያስበለጣችሁ በእነርሱ ላይ አትገንቡ፥ነገር ግን ብሏቸው፥አጥብቃችሁ ያዟቸው።*"

"*ቃሌ እንድትመገቡትና ለሰዎች ጥቅም ነው እንጂ በላዩ ላይ እንድትገነቡ አይደለም። እንዲፈቀር (ጠበቅ ተደርጎ እንዲያዝ)። በአግባቡ (ከቃሌ) ስትካፈሉ፥ ፍሬው በድንገት ይወጣል። በውጭ የሚንጸባረቀው፥ በአግባቡ ስትካፈሉና በቃሌ ያለ ህይወት ነው። የሚታየው ያ ነው። የመሰጠት ህይወት ነው በሁሉም የሚታየው። በብዙዎች የተጠላ ነው።*"

"*እኔ ሙሉ በሙሉ ስታይ፥ያኔ እውነተኛ ለውጥ መጥቷል።*"

"*ይህ ቤት የእኔ ቤት ነው። ከእናንተ በፊት በነበሩ ብዙ ትውልዶች መሠረት ላይ የተገነባ ነው። ብዙ የክብር ቀናትን አይቷል፥እንዲሁም ብዙ የሽንፈት ቀናቶችንም አይቷል። አሁን በውድቀት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው፥ አንዳንድ ቦታዎች ደግሞ በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ፥ እናም በእርሱና በውስጡ የሚያልፉት ግርግዳዎቹን አያጠነክሩም፥ መግቢያዎቹንም አያጸዱም አያድሱምም። የሚጨነቁት ስለራሳቸው የሥራ ጉዳይ ነው እንጂ ስለእኔ ቤት አይደለም። መለወጥ አይፈልጉም። ያ አሁን ይለወጣል።*"

"*እውነተኛ በር ጠባቂዎችን እያመጣሁ ነው እናም እነርሱ መግቢያዎቹን ይጠግናሉ።*"

"*በዚህ ሰዓት በእኔ ያልተገነባውን ሁሉ እያፈረስሁ ነው፥ ቤቴ ወድቆና በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የትኛውም ሰው የሠራው ቤት አይጸናም። እያንዳንዱ መሠረት ይጋለጣል። እኔ የቤቴ ጌታ ነኝ፥ እናም ለእኔ ጥቅም የሚመጥን ቅዱስ ቤት ይኖረኛል።*"

"*በእውነትን ፍለጋችሁ ላይ ደስተኞች ሁኑ፥ እኔንም አጥብቃችሁ ያዙኝ። ቃሌም የበለጠ በእናንተ ውስጥ እንዲሠራ ፍቀዱለት፥ ከእርሱም አብዝታችሁ ተመገቡ። ቃሎቼ በእናንተ ቢኖሩ፥ ያኔ እኔ የበለጠ ወደ ውስጥ እመጣለሁ፥ እናም ለእኔ ብዙ ክፍል ስታዘጋጁልኝ፥ ከእናንተ ጋር እራት መብላቴን እቀጥላለሁ፥ እንዲሁም ከአባቴ ጠረጴዛ ላይ ሥጋውን ከእናንተ ጋር እካፈላለሁ። ሥጋው የሚሰጠው ዳቦን ብቻ ለሚሹት ስላይደለ። ሙሉ በሙሉ ለእኔ ለተሰጡት(ለተማረኩት) ነው የሚሰጠው።*"

ጌታ ከዚያ በኋላ ዞረና በሩን ገፍቶ ከፈተው፥ከዚያም ወደታጠረችው ከተማ ገባ።

- በሱዛን ከሚንግስ፤ እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 18፥2005 ሌሊት 9፡38

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com